

የዕለተ ፡ እሑድ ፡ የቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ ገድል።

፩ ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ በተቀደሰች ፡ ዕለተ ፡ እሑድ ፡ የሚነበብ ፡ የያሬድ ፡ ካህን ፡ ገድል ፡ የቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ ካህን ፡ ጸሎትና ፡ በረከት ፡ ከባሮቹ ፡ ከ ና ፡ ከ ጋር ፡ ይኑር ፡ ለዘለዓለሙ ፡ አሜን።

፪ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሰሎሞን ፡ ላይ ፡ የኤዶም ፡ ወገን ፡ ሰይጣን ፡ አዴርን ፡ አቆመ ፡ እንደተባለ ፡ ግን ፡ የምድር ፡ ጨዋታና ፡ ዘፈን ፡ አይደለም ፡ በመንበሩ ፡ ዙርያ ፡ እየጠራ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚያመሰግኑበት ፡ የሱራፌል ፡ ምስጋና ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ድንቅ ፡ ነው ፡ እውነት ፡ ከጽርሐ ፡ አርያም ፡ ተምረዋልም ፡ ተቀብሏልም።

፫ ፡ ስለዚህ ፡ ማኅሌቱ ፡ ሰማያዊ ፡ ነው ፡ ተባለ ፡ እኛም ፡ የያሬድ ፡ ካህን ፡ ማኅሌት ፡ ከምድር ፡ እንዳልሆነች ፡ እንወቅ ፡ እንመን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ከሰማያት ፡ ካልሆነ ፡ በስተቀር ፡ ከሃያ ፡ አራቱ ፡ ካህናተ ፡ ሰማይ ፡ እንደተማረ ፡ የቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ ካህን ፡ በረከቱና ፡ ተራዳእነቱ ፡ ከባሮቹ ፡ ከ ና ፡ ከ ጋር ፡ ይኑር።

፬ ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ በአብና ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅድስም ፡ ስም ፡ ንጹሕና ፡ የተመሰገነ ፡ ንኡድ ፡ ክቡር ፡ የሚሆን ፡ የያሬድ ፡ ካህን ፡ ገድልና ፡ ምሥክርነት ፡ በረከቱ ፡ ከባሮቹ ፡ ከ ና ፡ ከ ጋር ፡ ይኑር ፡ ለዘለዓለሙ ፡ አሜን።

፩ ፡ ከሰይጣን ፡ ጋር ፡ እንደተጋደለ ፡ እንነግራችኋለን ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ እየተገዛ ፡ እንዳሸነፈ ፡ በብዙ ፡ ምስጋናው ፡ እንደሱራፌል ፡ ሲያመሰግን ፡ ነቢዩ ፡ ኢሳይያስ ፡ ያየውና ፡ የሰማው ፡ በከፍታ ፡ የከበሩ ፡ እንያ ፡ ሱራፌል ፡ እግዚአብሔርን ፡ በሰማይ ፡ ሲያመሰግኑት ፡ እነዚያም ፡ ካህናተ ፡ ሰማይ ፡ ናቸው ፡ ከሰይጣን ፡ ጋራ ፡ ተጋደለ ፡ ትጉሃን ፡ መላእክት ፡ በምስጋና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ምስጋናን ፡ እየሰማ ፡ አሸነፈ ፡ ዮሐንስ ፡ ወልደ ፡ ነጐድጓድ ፡ እንዳየ

፪ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እንደብዙ ፡ ሰው ፡ በሰማይ ፡ ታላቅ ፡ ድምጽ ፡ ተሰማ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፡ አለ ፡ ምስጋና ፡ ለአምላካችን ፡ ይገባልና ፡ ፍርዱ ፡ እውነት ፡ ነውና እንደገናም ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፡ ይላሉ ፡ ጭስም ፡ ለዓለም ፡ ወጣ ፡ ሃያ ፡ አራት ፡ ካህናተ ፡ ሰማይም ፡ ሰገዱ ፡ ሊቃውንትም ፡ ከመንበሩ ፡ ላይ ፡ የሚኖር ፡ የእግዚአብሔር ፡ እንያ ፡ አራት ፡ እንስሳዎቹም ፡ ትልቆቻችሁ ፡ ትናንሾቻችሁ ፡ ሁላችሁ ፡ የምትፈሩት ፡ ባሮች ፡ አምላካችንን ፡ አመስግኑት ፡ የሚሉ።

፫ ፡ እንደገና ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፡ አሉ ፡ ሁሉን ፡ የሚገዛ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነግሷልና ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ ይበለን ፡ ለሱም ፡ ምስጋና ፡ እንስጥ ፡ በልጁ ፡ ሠርግ ፡ አዳራሽ ፡ ንጹሕ ፡ የሆነ ፡ የብርሃን ፡ ልብስን ፡ እንደ ፡ ልብስ ፡ የተሠጣት ፡ ሴት ፡ የተዘጋጀች ፡ ናትና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃልና ፡ ምስጋና ፡ በሬዛሽትና ፡ በታላቅ ፡ ድምጽ ፡ እንድሆነ ፡ ረአዬ ፡ ኅቡአት ፡ ዮሐንስ ፡ የሚለውን ፡ ስሙ ፡ የምስጋና ፡ የቅዱሳን ፡ የጻድቃኖች ፡ ልብስ ፡ ነውና።

፰ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ብዙ ፡ ሰውና ፡ እንደ ፡ ታላቅ ፡ ነጐድጓድ ፡ ድምጽ ፡ ቃልን ፡ ሰማሁ ፡ ያሬድ ፡ ካህንም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ምስጋናን ፡ ያመሰግናል ፡ በሚገርምና ፡ በታላቅ ፡ ድምጽ ፡ እያመሰገነ ፡ ነው ፡ ጌታችን ፡ በመጽሐፉ ፡ ኪዳን ፡ እንግዲህ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ በታላቅ ፡ ድምጽ ፡ ያመስግነው ፡ እንዳለ ፡ ያሬድ ፡ ካህንም ፡ እንደ ፡ ትጉሃን ፡ መላእክት ፡ ይመሰላል ፡ ሐዋርያት ፡ በመጽሐፋቸው ፡ እንዳሉም ፡ በሬዙት ፡ ምስጋናን ፡ ተባበሩ ፡ ቅዱሳን ፡ የሚሆኑ ፡ ስድስት ፡ ክንፍ ፡ ያላቸው ፡ ሱራፌልና ፡ ኪሩቤልም ፡ በታላቅ ፡ ድምጽ ፡ አንተን ፡ ያመሰግናሉ ፡ በማያቋርጥ ፡ ቃልም ፡ ይዘምራሉ ፡ የተመሰገንክ ፡ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፡ የክብርህ ፡ ምስጋና ፡ በምድርና ፡ በሰማያት ፡ ፍጹም ፡ ምሉ ፡ ነው ፡ ሲሉ።

፱ ፡ በቀኞጥራቸውም ፡ እነዚህ ፡ መላእክት ፡ የመላእክትም ፡ አለቆች ፡ መናብርት ፡ ሥልጣናትም ፡ አጋዕዝትና ፡ ሊቃናትም ፡ ኪሩቤልና ፡ ሱራፌል ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ሲሉ ፡ ይጮኻሉ ፡ ያሬድ ፡ ካህንም ፡ ፊት ፡ በጠራነው ፡ ዜማ ፡ ዕዝል ፡ አንቀጸ ፡ ብርሃን ፡ አለ ፡ ክንድ ፡ ያህል ፡ ከመሬት ፡ ከፍ ፡ አለ ፡ ድንግልተ ፡ ሕሊና ፡ ድንግልተ ፡ ሥጋ ፡ ወደምትሆን ፡ እናታችን ፡ ማርያም ፡ ለመነ ፡ ለመጋደሉ ፡ ፍጻሜ ፡ ትረዳውና ፡ የሕይወት ፡ መንገድን ፡ ትመራው ፡ ዘንድ።

፲ ፡ ከዚህ ፡ በኋላም ፡ አለችው ፡ ቃል ፡ በቃልም ፡ ተናገረችው ፡ መቅደሴን ፡ እንዴት ፡ ትተዋለህ ፡ አለችው ፡ መቅደሴን ፡ ሰማያዊት ፡ አደረግሃት ፡ ስትል ፡ በማኅሌት ፡ ምስጋና ፡ የኪሩቤልና ፡ የሱራፌል ፡ ወገን ፡ ያደረግኋቸው ፡

ልጅቹንም ፡ ዳግመኛም ፡ መንገዱን ፡ እስክትሸኘው ፡ በዕንባና ፡ በልቅሶ ፡ ለመነ ፡ (ጸለየ)።

፲፩ ፡ ከዚህ ፡ በኋላም ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወጣ ፡ ገነትን ፡ የሚያጠጡ ፡ አራት ፡ ወንዞች ፡ ከነዚያ ፡ አንድ ፡ የሆነ ፡ የተከዚ ፡ ውሀ ፡ ድረስ ፡ የድንኳን ፡ ካህናት ፡ እየሸኙት ፡ ሄደ ፡ ኤፌሶን ፡ የተባለ ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ይሄዳል ፡ ከሱ ፡ በመለያየታቸው ፡ ጊዜም ፡ ሬኽ ፡ ሰላምን ፡ ተቀበልን ፡ ሰላምንም ፡ ለናንተ ፡ ተውን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰላምም ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ ይሁን ፡ አለ።

፲፪ ፡ እንደገናም ፡ ሁሉ ፡ ያለባት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰላም ፡ ሁሉ ፡ ጊዜ ፡ ከሁላችሁ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ካህናትም ፡ ይህንን ፡ ሰምተው ፡ መራራ ፡ ልቅሶን ፡ አለቀሱ ፡ እሱም ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ አለቀሰ።

፲፫ ፡ ከዚህ ፡ በኋላም ፡ ለየብቻቸው ፡ ተሰነባበቱ ፡ እነሱም ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ተመለሱ ፡ ያ ፡ ያሬድ ፡ ካህንም ፡ ምድረ ፡ ጸለምት ፡ ወደሚባል ፡ የሰሜን ፡ በረሃ ፡ ሄደ ፡ በዛም ፡ በትጋት ፡ በጸም ፡ በጸሎት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ነበረ ፡ በብዛት ፡ ስብሐተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሱራፌል ፡ እንደተማረው ፡ የሰሜንና ፡ የጸለምት ፡ ሰዎችን ፡ እያስተማራቸው ፡ ወደሱ ፡ የመጡ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ምስጋናን ፡ ያስተምራል ፡ እኛ ፡ ሁላችን ፡ የትምህርቱ ፡ ልጆች ፡ ነንና።

፲፩ ፡ ከብዙ ፡ ዘመናት ፡ በኋላም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ካህናት ፡ አወጡት ፡ እጅም ፡ ነሱለት ፡ ፊቱ ፡ አለም ፡ ሰላም ፡ ለናንተ ፡ ይሁን ፡ በሰላምም ፡ እጠይቃችኋለሁ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ደህና ፡ ናቸው ፡ ወይ ፡ ጽዮንም ፡ እጅ ፡ ትነሣላቸኋለች ፡ እጅ ፡ መንሻም ፡ ሰላምታ ፡ ነው።

፲፪ ፡ ሁለተኛም ፡ ወንድሙ ፡ ገበኘው ፡ ፊቱ ፡ አለም ፡ ወንድሜ ፡ ሰላም ፡ ላንተ ፡ ይሁን ፡ ሰውነቴ ፡ የምትወድህ ፡ ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ ሰላም ፡ ላንተ ፡ ይሁን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰላምም ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ ይሁን።

፲፫ ፡ ቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ ካህን ፡ ግን ፡ ገድሉን ፡ በሰሜን ፡ ምድርን ፡ ፈጸመ ፡ አረፈም ፡ ሥጋውም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ በምሥራቅ ፡ በሰሜን ፡ አለ ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለፈቀደለት ፡ ካልሆነ ፡ በስተቀር ፡ ለማንም ፡ ሳይገለጥና ፡ ሳይታወቅ።

፲፬ ፡ በኋላኛው ፡ ለትም ፡ ያሬድ ፡ ካህን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ካመሰገኑት ፡ ካህናተ ፡ ሰማይ ፡ በተቀበለው ፡ ዜማ ፡ ቁሞ ፡ ያስተምራል ፡ እንደሱም ፡ ደማቸው ፡ የፈሰሰ ፡ መነኰሳትና ፡ ጻድቃን ፡ ሕፃናትም ፡ በሀገሩ ፡ ደብረ ፡ ጽዮንና ፡ በመቅደሱ ፡ ከያሬድ ፡ ካህን ፡ ጋራ ፡ ያመሰግኑታል ፡ ምድርም ፡ አደራዋን ፡ ስትመልስ ፡ ፀሐይ ፡ ጨረቃ ፡ በሚጨልሙ ፡ ጊዜ ፡ ወልድ ፡ መንግሥትነቱን ፡ ከአብ ፡ መንግሥትነቱን ፡ በተቀበለ ፡ ጊዜ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ጌታ ፡ ለንጹሐንና ፡ ለካህናት ፡ ያስቀምጠዋል ፡ ያሬድ ፡ ካህንም ፡ ከፊቱ ፡ በፊቱ ፡ ቁሞ ፡ ያመሰግናል ፡ የቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ ካህን ፡ ጸሎትና ፡ በረከት ፡ ከአገልጋዮቹ ፡ ከ
ና ፡ ከ ጋር ፡ ይኑር ፡
ለዘለዓለሙ ፡ አሜን።

፲፱ ፡ ቅዱስ ፡ ያሬድም ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላኩን ፡ አለው ፡ መታሰብያየ ፡ ያደረገ ፡ ደመወዙ ፡ እንግዲህ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ በመንግሥቴ ፡ ማልኩ ፡ አለው ፡ ከፈተኛው ፡ የአንድ ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ምሳ ፡ (ምግብ) ፡ እንዳስቀምጠው ፡ በኋለኛይቱ ፡ ቀንም ፡ ያለፍርኃት ፡ በግልጥ ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ያልፋል።

፳ ፡ መታሰብያህን ፡ ያደረገ ፡ የገድልህ ፡ መጽሐፍን ፡ ያጻፈ ፡ ብፁዕ ፡ ነው ፡ እኔ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ እሰጠዋለሁ ፡ የክብር ፡ መንበርንም ፡ አወርሰዋለሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህንን ፡ ኪዳን ፡ ከሰጠው ፡ በኋላም ፡ በተሸሸገ ፡ (በተሠወረ) ፡ ሁኔታ ፡ በሰሜን ፡ በረሃ ፡ በስተምሥራቅ ፡ በሰላም ፡ አረፈ ፡ የቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ ካህን ፡ ጸሎት ፡ በረከት ፡ ከባሮቹ ፡ ከ ና ፡ ከ ጋር ፡ ይኑር ፡ ለዘለዓለሙ ፡ አሜን።

ተአምር ፡ በል ፡ ማክሰኞ ላይ ገጽ ፶፱ አለ።